# ተሐድሶው ይትጋ !!

ይነበብ ይግለጡ 05-16-17

ተሀድሶው ከተጀመረበት ግዜ ጀምሮ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል እንዴትስ እየሄደ ነው የሚሉ ጥያቄዎች በስፋት ይደመጣሉ፡፡ጥልቅ ተሀድሶው ሰአትና የግዜ ገደብ የለውም፡፡ሂደቱ ተከታታይ ስራና እንቅስቃሴ መሆኑን ብዙዎች በቂ ግንዛቤ ያገኙበት አይመስልም፡፡ለጥልቅ ተሀድሶው መነሻ ምክንያቶቹ በውል ተለይተው የሚታወቁ ናቸው፡፡

በኢሕአዴግ ውስጥ የጥገኛና የሙሰኛው የኪራይ ሰብሳቢው ኃይል መንሰራፋት ጠባብነትና ትምክህት መጠንና ደረጃቸው በተለያየ መልኩ ገነው መውጣታቸው ይህም በተደረሰበት ሀገራዊ የእድገት ደረጃ መጠን ለድርጅቱ አሳሳቢ አደጋ እየሆነ መምጣቱ የህዝብን ቅሬታና ተቃውሞ መቀስቀሱ ፈጣን ምላሽና ውሳኔ የሚያስፈልገው ሁኖ መገኘቱ በመነሻነት የሚወሰዱ ናቸው፡፡ የሕብረተሰብ እድገት ሕግጋት እንደሚያስረዱት ለውጥና እድገት በመጣ ቁጥር ሁኔታዎች በፈጣን መልኩ ይለዋወጣሉ፡፡

አንድ ቦታ ተቸክሎ የሚቆይ ወይም ባለበት የሚቆይ ሁኔታ አይኖርም፡፡ያንን በአዲስ መልክ የተከሰተ ለውጥ የሚሸከም ወቅቱን የተከተለ አመራርና አስተዳደር ግድ ይላል፡፡የሕብረተሰብ እድገት በሀገራዊ ኢኮኖሚው በፖለቲካውም ሆነ በቴክኒዮሎጂው በትምህርቱም ሆነ በተለያዩ መስኮች ይከሰታል፡፡ እድገትና ለውጥ ራሱን ችሎ ይዞ የሚመጣቸው አዳዲስ ጥያቄዎች ይፈጠራሉ፡፡የትምህርና የቴክኒዮሎጂው እውቀትና እድገት ሕብረተሰቡን የነቃና የበቃ ያደርገዋል፡፡

ጠያቂ ለምን ባይ ሞጋችና ለመብቱ ተከራካሪ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የላቀ ሚና ይጫወታል፡፡በድሮ በሬ ያረሰ የለም እንዲሉ ትላንት የነበረው አስተሳሰብና እምነት አካሄድ በብዙ መልኩ የሚቀየርበት ሁኔታም ይፈጠራል፡፡ የግድ ግዜውን ዘመኑንና እድገቱን መከተል ይጠበቅበታል፡፡ይህ ካልሆነ ኃላፊነትን መሸከምና መምራት አዳጋች ይሆናል፡፡

ተሀድሶው የአዲስ ለውጥ ጅማሬ ነው፡፡ድሮ እንዲህ ነበርን በዛው እንቀጥል የማይባልበት ወቅትን ግዜን የሕብረተሰብን እድገት ተከትሎ ለወቅቱ የሚመጥን አዲስ አሰራርና አመራር መፍጠርንም ይጠይቃል፡፡ሙስናውና ኪራይ ሰብሳቢነቱ አድጎ የተንሰራፋው በመንግስታዊና በፓርቲው አመራር ከላይ እስከ ታች ባሉት ውስጥ በመሆኑ ይህንን

የተሰጠውን ኃላፊነት ተጠቅሞ ሕብረተሰቡን ለምሬትና ለአመጽ ያበቃውን ያንገሸገሸውንና ያስመረረውን የውስጥ ጥገኛ ኃይል (ፓራሳይት) የግድ ማጥራትና ከኃላፊነቱ ማንሳት የነበሩ አሰራሮችን ፈትሾ መቀየር መለወጥ የሕብረተሰቡን ጥያቄ አቅም በፈቀደ መጠን በፍጥነት መመለስ የሕብረተሰቡ እድገት ያመጣውና የወለደው በመሆኑ ለዚህ ተዘጋጅቶ መስራትን ይጠይቃል፡፡

ይህንን ማድረግ ካልተቻለ መምራት የሚገባው ተመሪ ሁኖ የጋሪው ከፊት መቅደም የፈረሱ ከኃላ መሆን አይነት ዝብርቅ ይፈጠራል፡፡ትልቁ ነጥብ ተሀድሶው በግዜ ሰሌዳ በዚህ ቀን ተጀምሮ በዚህ ቀን ያልቃል ተብሎ ቀመር የሚወጣለት አይደለም፡፡ ቋሚ ሁኖ ይቀጥላል፡፡

ለምን ቢሉ ሁልግዜም በሕብረተሰቡ ውስጥ አዳዲስ ግዜውን ተከትለው የሚመጡ ለውጦች እድገቶች አሉ፡፡ይህ ደግሞ የሕብረተሰብ እድገት ሕግ የሚያመጣው ስለሆነ በነዚህ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ውስጥ እየበቁ ስሕተትን እያረሙ እየታደሱ ግዜውና ወቅቱ በሚመጥነው መልኩ መራመድ ግድ ስለሆነ ነው፡፡በበርካታ ሀገራት ይህ ተሞክሮ ታይቶአል፡፡

ፍጹም የሚባል ነገር ፍጹማዊ የሚባል የመንግስት አስተዳደር አመራር አሰራር በምድር ላይ የለም፡፡ ስህተቶችን ሁልግዜም እንደ መንግስትም እንደ ፓርቲም እያረሙ መሄድ የሕብረተሰቡን ጥያቄ መመለስ ወቅትና ግዜዎችን ተከትሎ በፈጣን ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ውስጥ የሚከሰቱትን ችግሮች መፍታትን ከድክመት ተምሮ ጥንካሬን ማጎልበት ስህተትን ማረም የበለጠ ለመስራት መንቀሳቀስ የነበረና ያለ በመሆኑ ነው፡፡

ተሀድሶ ለውጥና የለውጥ ሂደት ነው፡፡በቃ እዚህ ጋ ይቆማል የሚባል አይደለም፡፡ሁሌም በለውጥ ውስጥ ይተማል፡፡ለውጡም እንደገና አዲስ ለውጥ ይዞ ይመጣል፡፡ይቀጥላል፡፡ በአንድ ቦታ ብቻ ተቸክሎ የሚቀር የሕብረተሰብ እንቅስቃሴና እድገት የለም፡፡ በቀጣዩ ወደ ተሻለ ምእራፍ ይሸጋገራል፡፡የተሐድሶው መሰረታዊ አላማ በአገሪቱ የተጀመረውን ለውጥ ማስቀጠል ሲሆን የተመለሱ በሂደትም የሚመለሱ የሕዝቡ ጥያቄዎች አሉ፡፡በአንድ ጀምበር ሁሉንም መከወን አይቻልም፡፡ተሀድሶው ሂደትም ነው፡፡

ተሀድሶው የራሱን የግዜ ሂደት ይጠይቃል፡፡በተሀድሶው አልፈው ያልታደሱ የጠባብነትና የትምክህት የጎጠኝነት በሽታ የተሸከሙ ዛሬም አሉ፡፡ይሄም ለራሱ ለፓርቲው ትልቅ ፈተና ነው፡፡በሂደት ማጥራት ይጠበቅበታል፡፡

አንድ አሮጌና ኃላቀር አስተሳሰብን በውስጣቸው ያደበሩ ያጎለበቱ ግለሰቦች ታድሰናል ቢሉም ሊታደሱ የሚችሉበት መሰረት የላቸውም፡፡ለማምለጥና ለመመሳሰል እስካልሆነ ድረስ በመታደስ ስም ያለፉ ገና መታደስና መለወጥ የሚቀራቸው ለራሱ ለድርጅታቸውም መስመር በፈታኝነት የሚቀርቡ ግትርና አክራሪ ኃይሎች የሉም ለማለት አይቻልም፡፡ ኢሕአዴግ ራሱን እነዚህን ከመሰሉ ኃይሎች እስካላጠራ ድረስ ተሀድሶውን ሊቀለብሱት ይችላሉ፡፡

ኢሕአዴግ ሕዝቡን ከጎኑ በማሰለፍ ትግሉን በስፋት መቀጠል አለበት፡፡እንዳለውም የጥልቀታዊው ተሀድሶ ባለቤት ሕዝቡና ሕዝቡ ብቻ ነው፡፡ሀገርን የለወጠ ታላቅ የመሰረተ ልማት ግንባታን ያካሄደ ትውልድና ዘመን ተሻጋሪ ስራዎችን የሰራ ድርጅት ነው ኢህአዴግ፡፡እየሰራም ይገኛል፡፡በሙስና በኪራይ ሰብሳቢነት በጥገኛነት በመልካም አስተዳደርና በፍትህ ረገድ ችግር ሲፈጥሩ የነበሩትን  በአደባባይ በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ከሕዝብ በታች እንጂ ከሕዝብ በላይ እንዳልሆኑ ሊያውቁትም ሊረዱትም ይገባል፡፡የሀገሩ ባለቤት ሕዝብ ነው፡፡

ሌላው ብሔራዊ ስሜትን ሸርሽረውት በቆዩ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ተሀድሶው ሊሰራ ይገባዋል፡፡መንግስት የገባውን ቃል አክብሮ እየሰራ መሆኑ ቢታይም ዛሬም ብዙ ያልተፈቱ ያልተመለሱ ጥያቄዎች እንዳሉ ያውቃል፡፡እነዚህን ለመመለስ በብቃት መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል፡፡በጥልቀት የመታደሱ ሂደት አዲስ ጅማሮ ቢሆንም በስፋት ሊቀጥል የሚገባው ነው፡፡

በቢሮክራሲው ውስጥ የመሸገው አድፋጭ ሙሰኛ ኃይል ለግዜው ጭራውን የቆለፈ መስሎ ቢሸሸግም አልተነካም የሚለው የሕዝብ አስተያየት ሚዛን ይደፋል፡፡በሕዝብ ሀብትና ንብረት መቀለዱንም አላቆመም፡፡በእርግጥ ኢሕአዴግ ከሕዝብ ጋር እንዲጋጭ እንዲጣላ እንዲናቆር ያደረጉት በከፋ ራስወዳድነትና ስግብግብ በሆነ የጥቅም ስሜት የታወሩ ፈሪሀ

ሕዝብ የሌላቸው ይሉኝታን የማያውቁ የራሱ ጉዶች ናቸው፡፡የጀመረውን ምንጠራ መቀጠል አዋጪው ነው፡፡

ኢሕአዴግ የሰራውን ግዙፍ ሕዝባዊ የተሳካ ስራ ሁሉም ሕዝብ ቢያውቀውም ይህቺ ሀገር የማናት እስከሚል ድረስ ያደረሱት ሕዝቡን እያማረሩ ለብጥብጥና ለአመጽ የዳረጉት የሁሉም ነገር መነሻዎች የራሱ አባላት የነበሩት ናቸው፡፡ኢጋጣሚውን ለመጠቀም ተደርቦ የመጣው ኃይል ዋናው መነሻ ሳይሆን በሁለተኛ ደረጃ የሚወሰድ ነው፡፡ዋናው ጉዳይ ያለው በራሱ በውስጥ ነው፡፡
አሁንም ጅምሩ ተሀድሶ እንዳይቀለበስ ኢሕአዴግ ከሕዝቡ ጋር ያለውን ትስስር በማስፋት ሙሰኞችና ኪራይ ሰብሳቢ ኃይሎችን የመመንጠሩን ዘመቻ ለራሱም ህልውና ሲል መቀጠል አለበት፡፡የሕዝብ ቃል የአምላክ ቃል እንዲሉ፡፡ተሀድሶው ተጀመረ እንጂ ገና እልፍ አላለም፡፡እልፍ እንዲል የሕዝቡ ንቁ ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡

የተጀመሩትን ታላላቅ ሀገራዊ ሜጋ ፕሮጀክቶች ለማስቀጠል ተሀድሶው ያለው ፋይዳ የገዘፈ ነው፡፡በሀገሪቱ ልማትና እድገት ላይ መደራደር አይቻልም፡፡ዘራፊዎችንም በዝምታና በአርምሞ ማየት አብቅቶአል፡፡አንዱ ሕዝቡ በስፋት የሚያነሳው ጥያቄ በቢሊዮኖች በተዘረፈባት ሀገር ላይ በሕግ ተጠያቂ የሚሆን አካል መጥፋቱ ዛሬም ቁስሉን አላጠገገውም፡፡የሕዝቡ ዝምታ እንደ ዘላቂ ሰላም ሊወሰድ አይችልም፡፡ችግሮችን ከመሰረቱ ስርነቀል በሆነ ሁኔታ ለመከላት ኢህአዴግ የመጨረሻ ውሳኔ መስጠት ከቻለ ሁኔታዎች መልካቸውን ሊቀይሩ ይችላሉ፡፡አስተማማኝና ዘላቂ ሰላም ይኖራል፡፡

የትኛውም ሀገር ላይ ዘረፋ ያካሄዱ በመንግስትና በሕዝብ ሀብት ላይ የተጫወቱ የተሰጣቸውን መንግስታዊ ኃላፊነት ተጠቅመው ሀብት በማግበስበስ ስራ የተጠመዱ ለህግ ይቀርባሉ፡፡በአዲስ አበባና ከአዲስ አበባም ውጭ የባለብዙ ሀብት ባለቤት ለመሆን የበቁ በሁሉም ክልሎች ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን በሕዝብ ፊት ለሕግ ማቅረብ ሕዝቡን የበለጠ እምነት እንዲጥል እንዲገነባ ያደርገዋል፡፡የድርጅቱንም ጥረትና ልፋት ሕዝቡ ሊረዳው ይችላል፡፡
ለሀገሪቱ ሰላምና መረጋጋትም ትልቁን ድርሻ የሚወጣው ሕዝብ ነው፡፡ተሀድሶው ተስፋ ሰጪ ነው የሚሉ የመኖራቸውን ያህል ተሀድሶው ኢህአዴግ የራሱን ቁንጮ ባለስልጣናት

ሸሽጎ የታችኛውን አካል ነው የወረደበት የሚሉም አሉ፡፡ተሀድሶው ተስፋ ሰጪ እርምጃዎች እንዳሉት የታመነ ነው፡፡ተሀድሶው የሚቀረው በሙሰኞችና በኪራይ ሰብሳቢዎች ላይ ወሳኝ እርምጃዎችን በመውሰድ ለሕዝብ የጸና እምነቱን ማረጋገጥ ነው፡፡

የታችኛው ሙሰኛና ኪራይ ሰብሳቢ ጥገኛ ኃይል በምንም ተአምር ከላይኛው ጋር ሳይቀናጅ እራሱን ችሎ ሰፊ የሙስና መረብ ውስጥ መግባት አይችልም፡፡አይዞህ ባይና የሚሸሸግበት ዋሻ ያስፈልገዋል፡፡የታችኛው ላይ የተወሰደው እርምጃ በደረጃ ከፍ ያሉትም ላይ መቀጠል አለበት የሚለው የሕዝብ አስተያየት ሊሰመርበት ይገባል፡፡ሚዛንም ይደፋል፡፡

በጥልቀት የመታደስ ሂደት ተጨባጭ ለውጦችን ማስመዝገብ አለበት፡፡የአስተሳሰብ ለውጥን በማምጣት መልካም አስተዳደርን ማስፈን መቻል ገድ ነው፡፡ሌላው በተሀድሶው የመጀመሪያ ወቅቶች ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የፖለቲካና የመንግስትን ስራዎች ተለይተው እንዲሰሩ እንደርጋለን ያሉት አሁንም ተግባራዊ ሁኖ አልታየም፡፡የመንግስት ስራና የፖለቲካ ስራ ተለይቶ መቀመጥ ይገባዋል፡፡

ዜጎች ሀገሪቱ ባስተማረቻቸውና ባበቃቻቸው የእውቀት ደረጃ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ያላቸውን እውቀትና ችሎታ ተጠቅመው ለውጥ ለማምጣት ይስሩ፡፡ለኢሕአዴግ የጠቀሙና ያገለገሉ መስለው ከሕግና ከስርአት ውጪ የሚወራጩ ካድሬዎች ናቸው ለትላንቱም ችግር አቢይ መነሻዎች፡፡የካድሬዎች አላስፈላጊ ጣልቃገብነት በሙያተኞች ላይ መመረርና መሰቀቅን እንዳያመጣ መጠንቀቅ ያለበት መንግስት ነው፡፡

በተግባር መታረም በአመለካከት ከመታረም ውጪ ሊመጣ አይችልም የሚለው አገላለጽ ተገቢ ሁኖ ሳለ የአመለካከት ለውጥ በቀላሉ የሚደረስበት ስላልሆነ ተከታታይና ዘላቂ ስራዎችን ይጠይቃል፡፡ሀገራችን ይበልጥ ተጠቃሚ መሆን የምትችለው የተረጋጋና ዘላቂ ሰላም ባለቤት ሁና ልማትና እድገትዋን ማስቀጠል ስትችል ብቻ ነው፡፡ስሕተቶችን እያረሙ ሀገራዊ አቅምን እያጎለበቱ ለበለጠ ውጤት መስራት ተጠቃሚ የሚያደርገው የጋራ የሆነችውን ሀገር ሕዝብና መንግስትን ነው፡፡ተሀድው በጥንካሬ ወደፊት መጓዝ ይጠበቅበታል፡፡